# ዳንኤል ትምህርት ቤት ይወዳል




Amharic

ዳንኤል ትምህርት ቤት ይወዳል

ተጻፈ በኤልሳቤት ካርልሰን

ሥዕላዊ መግለጫ በዮሴፍ ዮሐንስ

የእንግሊዝኛ ትረካ በክሬግ ፋሮ

ምስሎች በዮሴፍ ዮሐንስ፣ © 2019 ዮሴፍ ዮሐንስ። CC BY-NC-SA 4.0.

ይህ ፕሮጀክት በግሎባል ፓርትነር ሺፕ ፎር ኢዱውኬሽን የተደገፈ እና በትምህርት ሚኒስቴር እና ቫኑዋቱ ስልጠና፣ ሴቭ ዘ ችልድረን እና ኤስ.አይ.ኤል ወደ እናንተ ቀረበ።

ቦርና

ኢትዮጵያ

የቅጂ መብት ያስፈልገዋል

# ዳንኤል ትምህርት ቤት ይወዳል

Amharic
Ethiopia

Copyright © 2025, SIL Ethiopia

http://creativecommons.org/licenses/by-nc-sa/4.0/
You may not use this work for commercial purposes. You may adapt and add to this work, but you may distribute the resulting work only under the same or similar license to this one. You must keep the copyright and credits for authors, illustrators, etc.

Written by Elizabeth Carlson
Translator: Samuel Daba
Illustrated by Joseph John
Images by Joseph John, © 2019



ይህ ዳንኤል ነው፣ ትምህርት እጅግ በጣም ይወዳል።



ዳንኤል መቼም ከትምህርት

አይቀርም። ፊደላትን እና

ድምጻቸውን ጠንቅቆ ያውቃል።

ማንበብ ይወዳል።



አንድ ቀን፣ የዳንኤል ጓደኛ፣
“ወፎችን ለማደን እንሂድ ”
አለው፤ ዳንኤል ግን “አይ !፣
ትምህርት ቤት መሄድ አለብኝ”
አለ።



በማግስቱ ሌላ ጓደኛው ዳንኤልን
“እንሂድና እግር ኳስ እንጫወት።”
አለው። ዳንኤል ግን “አይ፣
አይሆንም፤ ትምህርት ቤት
እየሄድኩ ነው" አለው።



ዳንኤል በትምህርት ቤት
የሚያነባቸውን መጻሕፍት
ይወዳል። በአፍሪካ ስለሚኖሩ
ጦጣዎች እና ቀጭኔዎች እንዲሁም
በእስራኤል ስለሚኖሩ ግመሎች
ያነባል።




በትምህርት ቤት፣ዳንኤል በሌሎች

አገሮች ውስጥ ስላሉ ሰዎች

ያነባል። ስለ ሰለሞን ደሴቶች፣

ጃፓን እና አውስትራሊያ

መጽሐፎችን ያነባል።



ዳንኤል በራሱ ቋንቋ፣ በቢስላማ፣ በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሳይኛ እና በቻይንኛ ማንበብ ይማራል!



ዳንኤል ትምህርት ቤት በጣም
ይወዳል። እያንዳንዱን መጽሐፍ
በራሱ ትምህርት ቤት ውስጥ
ማንበብ ይፈልጋል!

Let's grow a library

Bloom®